Australian Human Rights Commission
*everyone, everywhere, everyday*

AHMARIC

# የአፍሪካ አውስትራሊያውያን: በሰብዓዊ መብቶችና ማሕበራዊ ጉዳዮችን ያካተተ ሪፖርት - ስለ ውይይት ማቅረቢያ ወረቀት አጭር መግለጫ

## ምን እንዳሰቡ ለማወቅ እንፈልጋለን

በሞላው አውስትራሊያ ውስጥ ስላሉት የአፍሪካ አውስትራሊያውያን የሰፈራ መላመድና ሰብዓዊ መብቶች በተመለከተ ታሪክ መስማት እንፈልጋለን።

በአውስትራሊያ ውስጥ በቀላሉ ለመላመድ ስለሚቀየሩ ነገሮች ምን እንደሆኑ የርስዎን ሃሳብ መስማት እንፈልጋለን።

የመጨረሻ ሪፖርት ሲዘጋጅ የርስዎን ሃሳብ በማካተት እንጠቀማለን። ለአገልግሎትና ውሳኔ አቅራቢ ሰዎችና ድርጅቶች የመጨረሻ ሪፖርቱ እንደሚያበረታታ ተስፋችን ሲሆን ስለዚህ ሌሎች አውስትራሊያውያን ስለ አፍሪካ ማህበረሰባት ያላቸውን ግንዛቤ እንዲቀይሩ ይረዳል።

## የውይይት ወረቀቱ ምን ያደርጋል?

ለአፍሪካዊ አውስትራሊያውያን መረጃ ማቅረብና መጠየቅ እንዲሁም (ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው) ስለ እነሱ ታሪክ፣ ጉዳይና አሳሳቢ ሁኔታ እንዲነግረን ነው።

## ምን ማለት ይችላሉ?

ለአፍሪካዊ አውስትራሊያ ማህበረሰባት የሚመለከቱ ጉዳዮች በሰብዓዊ መብቶችና ማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲካተት የርስዎ ልምድና አስተያየት ሊረዳን ይችላል።

በአውስትራሊያ ውስጥ ስለ ሥራና ስልጠና፣ ትምህርት፣ ጤና ጥበቃና ደህንነት፣ የመኖሪያ ቤት፣ የፍትህና ህጋዊ በሆነ የአሠራር ዘዴዎች ያለዎትን ልምድ በተለይ ከርስዎ ለመስማት እንፈልጋለን። በተጨማሪም ስላለዎት ማንኛውም ጉዳይ ወይም አሳሳቢ ሁኔታ እንዲነግሩን እንፈልጋለን።

## ታሪክዎን እንዴት ሊነግሩን ይችላሉ?

- በሞላው አውስትራሊያ በምናቀናጀው ስብሰባዎችና ቡድኖች ላይ መምጣት (ለመሳተፍ ይረዳዎ ዘንድ በአንዳንዶቹ አስተርጓሚ ይኖራል)
- በጽሁፍ አድርገው ሃሳብዎን ለእኛ ማስገባት (ከዚህ በታች ያለውን መረጃ ይመልከቱ)

## ስለ ስብሰባዎች የት ሄጀ ማወቅ እችላለሁ?

- መረጃ ያገኙ ዘንድ የማህበረሰብ አውታሮች ይረዳሉ
- ዝርዝር ፕሮግራሙ ከመጋቢት/March 16 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በእንግሊዝኛ በድረ ገጻችን: www.humanrights.gov.au/africanaus ላይ ይቀርባል።

## ማን ነው የሚረዳን?

ፕሮጀክቱ በማህበረሰብ የሚመራና በተውጣጣ ኮሚቴና በአገር አቀፍ ማህበረሰብ በታወቁ ቡድኖች በኩል ድጋፍ ያገኛል። የሚመራው ኮሚቴ ሁለት ማህበረሰባትን ይወክላል: እነዚህም Samia Baho, ለአፍሪካዊ- አውስትራሊያኖች የሴቶች ጉዳይ ማእከል ዋና ዳሬክተር እና Abeselom Nega, የቀድሞ የፌደሬሽን አፍሪካዊ ማህበረሰባት ምክር ቤት መሪ; እንዲሁም የአገልግሎት አቅራቢ ተወካይ የሆኑት Eugenia Tsoulis, በሳውዝ አውስትራሊያ የማይግሬሽን መገልገያ ማእከል ዋና ዳሬክተር ናቸው።

የአገር አቀፍ መማክርት Myriad Consultants በተባለ ድርጅት አስተባባሪነት ይሆናል።

ሌሎች አጋሮችን የሚያካትተው: በቪክቶሪያ የጎልማሳ መድብለ ባህላዊ የትምህርት አገልግሎት (AMES); የአውስትራሊያ ቀይ መስቀል፣ በተለያየ የጤና ተቋም፣ በአውስትራሊያ መንግሥት የቤተሰብ ጉዳይ መምሪያ፣ የመኖሪያ ቤት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት እና የባለአገሩ ጉዳይን (FaHCSIA) ያካተተ ነው።

## ማስረጃን እንዴት አድርጎ እንደሚቀርብ

ያቀረቡት ማስረጃ በእንግሊዝኛ የተጻፈ ከሆነ በኢሜል: africanaus@humanrights.gov.au አድርገው ቢልኩልን እንመርጣለን።

በኢሜል መላክ ካልቻሉ ወይም ያቀረቡት ማስረጃ በራስዎ ቋንቋ ከተጻፈ በሚከተለው አድራሻ ይጻፉልን:

*African Australians project* submission
Race Discrimination Unit: Education and Partnerships Section
Australian Human Rights Commission
ፖ.ሳ.ቁጥር/GPO Box 5218
Sydney NSW 2001

ወይም በፋክስ ቁጥር: (02) 9284 9849 ይላኩት።

## ማስረጃ ለማስገባት የሚያበቃበት: 30 June 2009

## ሚስጢራዊነትን መጠበቅ

የሚቀርበው ማስረጃ በሚስጢር ይጠበቅልኝ ካላሉ በስተቀር ማንኛውም ማስረጃ እንደ ህዝባዊ የሆነ ሰነዶች ይያዛል። እባክዎ ማስረጃዎን በሚያስገቡበት ጊዜ ሚስጢራዊ ስለመሆኑ ይንገሩን።

## በበለጠ መረጃ እንዴት ማግኘት እንችላለን?

- እንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋንቋዎ ካልሆነ በማህበረሰብዎ ያሉትን ሌሎች ሰዎች እንዲረድዎ መጠየቅ ወይም በአካባቢ ማህበረሰብ ድርጅቶች መሞከርና ሰራተኛ ስለሚኖር ሊረዱ ይችላሉ።
- በድረ ገጻችን www.humanrights.gov.au/africanaus ላይ ማየት
- ያለዎትን ጥያቄዎች በኢሜል africanaus@humanrights.gov.au አድርገው ይላኩልን
- ስለሚኖርዎት ጥያቄ በስልክ (02) 9284 9600 ወይም 1800 620 241 (መናገርና መስማት ለተሳነው/TTY) አድርገው ያነጋግሩን።

## የአድልዎ መፍጠር ችግር አጋጥሞት ያውቃልን?

በአድልዎ መፍጠር ህግ በተጠቀሰው መሰረት ስለርስዎ መብቶች በበለጠ መረጃ ለማግኘት:

- በድረገጽ www.humanrights.gov.au/complaints_information/index.html ላይ ማየት
- በድረገጽን www.humanrights.gov.au/about/languages/index.html ላይ ማየት (በራስዎ ቋንቋ የተጻፈ መረጃ ወረቀት ከሌለ ያለዎትን ቅሬታ ለመግለጽ አስተርጓሚ ልናቀናጅልዎ ስለምንችል፣ ስለዚህ እባክዎ ይደውሉልን)
- በነጻ ለስልክ አስተርጓሚ አገለግሎት በቁጥር 131 450 በመደወል የራስዎን ቋንቋ መናገርና ከዚያም ከአውስትራሊያ ሰብዓዊ አገልግሎት ኮሚሽን ጋር በቁጥር 1300 656 419 ደውለው እንዲያገናኝዎ መጠየቅ።
- ለቅሬታ ማቅረቢያ የመረጃ መስመር በቁጥር 1300 656 419 መደወል።